# አክሊለ ፅጌ

አክሊለ ፅጌ ማርያም ቀጸላ መንግሥቱ
ለጊዮርጊስ(፪)
እኸ..ከበበ ጌራወርቅ(፪) አክሊለ ፅጌ

# Aklile Tsegie

Aklile tsegie maryam qetsela
mengistu legiyorgis(2)
ehee..kebebe geeraworq(2) aklile
tsegie

እንዘ ተሃቀፍዮ

እንዘተሃቅፍዮ ለሕጻንኪ ንኢ ማርያም

ንኢ ንኢ ንኢ ማርያም

**Enze tehakefyoo**

enzetehakefyoo lehetsanki

nei mariam

nei nei nei mariam

As you hold your baby please come to us

# የፅጌ ወረብ

ጽጌ  አስተርአየ ሠሪፆ እምአፅሙ። ለዘአምሃኪ

ድንግል (ጽጌ) ለገብርኤል በይነ(ምስለ) ሰላሙ (፪)

ወበእንተዝ ማርያም ሰበ ሐወዘኒ መዓዛ ጣዕሙ(፪)

ከበበ ጌራ ወርቅ ጽሩይ እምዕንቈ ባሕርይ ዘየኀቱ።

አክሊለ ጽጌ ማርያም ለጊዮርጊስ ቀጸላ መንግሥቱ።

## የጻድቃን እመቤት

የጻድቃን እመቤት የደናግል ተስፋ(፪)
ሀገር ለሀገር ዞረች አምላክን ታቅፋ
አምላክን ታቅፋ ስትዞር በበረሃ
እንባዋ ይፈሳል እንደክረምት ውሀ

Yetsadqan Emebet

Yetsadqan emebeat yedenagl tesfa(2)
heger leheger zorech amlaken taqfa
amlakn taqfa stzor bebereha
enbawa yifesal endekeremt wuha

መቼ ተስኖት ነው ውሀ ለርሷ ማውረድ
አስቦ ነው እንጂ ክብሩን ለማዋረድ
ሥልጣኑን ሸሽጎ ክብሩን ያዋረደው
ከገሃነም እሳት እኛን ሊያድነን ነው (፪)
meche tesnot newu wha lersua mawred
asbo new enji kibrun lemawared
seltanun sheshgo kibrun yawaredew kegehanem
esat egnagn liyadnen new

እንደ ክረምት ውሀ እንባዋ ሲወርድ
ምንም አላገኘች አይዞሽ ባይ ዘመድ
አይዞሽ ባይ ዘመዷ ወልደ አምላክ ሳለ
ውሀ ጥም ጸንቶባት አፏ ደርቆ ዋለ

endekeremt wuha enbawa siwared
menm alagegnech ayizosh bay zemed
ayzosh bay zemedua welde amlak sale
wuha tem tsentobat afuwa derqo wale

# ድንግል መከራሽን

ድንግል መከራሽን ጥቂት ላስታውሰው
በሄሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰው
አንቾ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት
እንደ ችግረኛ ተነሳሽ ስደት

ኧረ ለመሆኑ እንዴት አለቀልሽ
ስትንከራተቺ በረሃውን ቆርጠሽ
ይገሉታል ብለሽ ለልጅሽ አስበሽ
በሄሮድስ ዘመን <u>መከራሽን አየሽ(፫)</u>

አዛኚቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ
እንድትደርሽልኝ በመከራ ጊዜ
መከራን ያየሰው መቼም አይጨክንም
አትጨክኝብኝ <u>አደራሽን ማርያም (፫)</u>

አቤት የዛን ጊዜ ያየሽው መከራ
ያለቀሽው ለቅሶ ጭራሽ አይወራ
የአማኑኤል እናት አንቺ መከረኛ
እድሜሽን ጨርሽው ሆነሽ አዘንተኛ
ሀዘንተኛ ሆነሽ አዘንተኛ